301

# በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባላት ሰኔ 19/95

## ካደረጉት ሁለተኛ አስቸኳይ ስብሰባ

## የተጠናቀረ ቃለ ጉባኤ

*ሰኔ 1995*

*አዲስ አበባ*

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባላት ሰኔ 19/95

## ካደረጉት ሁለተኛ አስቸኳይ ስብሰባ

## የተጠናቀረ ቃለጉባኤ

ሀ. የስብሰባ ቦተ፣ ቀን ሰዓት

| | |
|---|---|
| የስብሰባ ቦታ፣ | ሆቴል ዲ አፍሪክ |
| የስብሰባ ቀን፣ | ሰኔ 19 ቀን 1995 ዓ.ም |
| የስብሰባ ሰዓት፣ | ጠዋት 3:30 - 6:30 |
| | ከሰዓት 9:00 - 11:00 |

ለ. በስብሰባው ላይ የተገኙ እና ያልተገኙ አባላት ዝርዝር

1. የተገኙ አባላት ዝርዝር

| | | |
|---|---|---|
| 1.1 ዶ/ር አብዱላሂ ሀሰን | የማዕከላዊ ስታቲክቲክስ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ | ሰብሳቢ |
| 1.2 የተከበሩ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ | የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤ | አባል |
| 1.3 የተከበሩ አቶ አሰፋ ብሩ | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊ | » |
| 1.4 የተከበሩ አቶ መለስ ማሪሞ | የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር | » |
| 1.5 የተከበሩ አቶ አባዲ ዘሞ | የትግራይ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር | » |
| 1.6 የተከበሩ አቶ ታደሰ ካሳ | የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ም/ዕርሰ መስተዳድር | » |
| 1.7 የተከበሩ አቶ አብዱልአዚዝ መሐመድ | የሐረሪ ሕዝብ ብ/ክ/መንግሥት ም/ዕርስ መስተዳድር | » |
| 1.8 የተከበሩ አቶ መሐመድ ጣሂሮ | የአፋር ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር | » |
| 1.9 የተከበሩ አቶ አብዲ ጆብሪል | የሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር | » |
| 1.10 አቶ አማረ ኢሳይየስ | የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊና የኮሚሽኑ ፀሐፊ | አባልና ፀሐፊ |

2. ያልተገኙ አባላት ዝርዝር

2.1 የጋምቤላ ሕዝብ ብ/ክ/መንግሥት ም/ቤት ፀሐፊ

2.2 የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር

2.3 የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

ሐ. ከኮሚሽን ጽ/ቤት እና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የተገኙ አባላት ዝርዝር

1. ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት የተገኙ

| | |
|---|---|
| 1.1 አቶ ገነነ ብዙነህ | የቫይታል ስታቲስቲክስ መምሪያ ኃላፊ |
| 1.2 አቶ ገበየሁ አበልቲ | የቴክኒክ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ |
| 1.3 አቶ አርጋው ይስራሽ | የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ኃላፊ |
| 1.4 ወ/ሮ ውድአላት ገዳሙ | የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ኃላፊ |

2. ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የተገኙ

| | |
|---|---|
| 2.1 ወ/ሮ ሣሚያ ዘካሪያ | ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 2.2 አቶ ይልማ አድማሱ | የመስክ ሥራ ክንውን መምሪያ ኃላፊ |

መ. የስብሰባው አጀንዳዎች

1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባላት የመጀመሪያ አስቸኳይ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ገምግሞ ማፅደቅ፣

   አቅራቢ:- አቶ አርጋው ይስራሽ

2. የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የቆጠራ ካርታ የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ ሪፓርት ማቅረብ፣

   አቅራቢ:- አቶ አማረ ኢሳይያስ

3. የኮሚሽኑ ጽ/ቤት አደረጃጀትና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት፣

   አቅራቢ:- አቶ ገነነ ብዙነህ

4. በ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራንና ሕዝባዊ ምርጫን በአንድ ወቅት ማካሄድን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት፣

   አቅራቢ:- የኮሚሽኑ ሰብሳቢና የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤ

5. በአቶ አሰፋ ብሩ የቀረበውን አማራጭ የሕዝብ ቆጠራ አሠራር በተመለከተ፣

   አቅራቢዎች:- አቶ አሰፋ ብሩ፣ የማ.ስ.ባ እና የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች

6. የቆጠራ ካርታ ሥራ የፋይናንስ ጥያቄና የመስክ ሥራ አደረጃጀት፣

   አቅራቢ:- አቶ ገበየሁ አበልቲ

7. በቆጠራው ካርታ ቀጣይ ተግባር ወቅት የኮሚሽኑን የሥራ መመሪያ የሚጠይቁ ጉዳዮች፣

   አቅራቢ:- አቶ አማረ ኢሳይያስ

8. ሌሎች ጉዳዮች ላይ መወያየት የሚሉት ናቸው።

በዚሁ መሠረት የኮሚሽኑ ሰብሳቢ (ዶ/ር አብዱላሂ ሀሰን) ለኮሚሽኑ አባላት እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ስብሰባውም በአንደኛው አስቸኳይ ስብሰባ ወቅት በተወሰነው መሠረት የተጠራ መሆኑን ገልፀው የቀረቡት አጀንዳዎችን ለቤቱ አስተዋውቀዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአጀንዳዎቹ ላይ የማስተካከያ ሀሳቦች ካሉ በሚል ጠይቀው ቤቱም በቀረበው አጀንዳ ተስማምቷል፡፡

በመቀጠልም በአጀንዳዎች ቅደም ተከተል ስብሰባው እንዲካሄድ አድርገዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የስብሰባው ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## አጀንዳ 1. የኮሚሽኑ አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ገምግሞ ማጽደቅ

ግንቦት 12/95 ከተካሄደው የኮሚሽኑ አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ አኳያ የተጠናቀረው ቃለጉባኤ በአጠቃላይ 13 ገጽ ያካተተ ሲሆን ይኸው ቃለጉባኤ በጽ/ቤቱ የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ኃላፊ አማካይነት ለቤቱ ተነቧል፡፡

የቃለጉባኤው ይዘትም የዕለቱ አጀንዳዎች፣ የስብሰባ ተሳታፊዎች ዝርዝር፣ በአጀንዳዎቹ ውይይት ወቅት የተነሱ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች'ን ያካተተ ሲሆን በዕለቱ ስብሰባም ውሳኔ ላይ መድረስ ያልተቻለባቸው እና በሚመለከታቸው አባላት አማካይነት ተገቢውን ማብራሪያና ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺ ሁኔታዎችን አመቻችቶ እንዲያቀርብ የተቀመጡ ዋነኛ ነጥቦችን በዝርዝር ያመለከተ ነበር፡፡

ቃለ ጉባኤው በንባብ ከተሰማ በኋላም የኮሚሽኑ ሰብሳቢ አስተያየትና ጥያቄ ካለ በሚል ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ ከቤቱም ቃለ ጉባኤው በአጠቃላይ በወቅቱ የነበረውን የውይይት ሂደት ያንፀባረቀና የተነሱ ጥያቄዎች፣ የተሰጡ ምላሾችና አስተያየቶች በተገቢው መልኩ ያካተተ መሆኑን የተገነዘበ ሲሆን በሚከተሉት ገጾች በሰፈሩት ሀረጐች/አረፍተነገሮች ላይ አንዳንድ ማሻሻያዎች/ ማስተካከያዎች አድርጓል፡፡

ማስተካከያ የተደረገባቸው ገጾችም

- ገጽ 4 የመጨረሻው ፓራግራፍ አራተኛ መስመር፡- «ከአባላቱም መካከል.......... ባቀረቡት ሀሳብ መሠረት ወደ ሁለተኛው አጀንዳ ተሸጋግሯል» የሚለው አረፍተነገር «ከአባላቱ መካከል..........ባቀረቡት ሀሳብ መሠረት ቃለ ጉባኤውን በማፅደቅ ወደ ሁለተኛው አጀንዳ ተሸጋግሯል» በሚል እንዲሻሻል

- ገጽ 9 ከአጀንዳው ቀጥሎ የመጀመሪያው ፓራግራፍ አራተኛ መስመር:- «የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤም .......... ይህን ያክል ግዙፍ የሆነ ጽ/ቤት ይኖረዋል የሚል ሳይሆን አንድ ዋና ፀሐፊ ብቻ ይኖረዋል የሚል መሆኑን አብራርተዋል» የሚለውን «.......... ጽ/ቤትና አነስተኛ የሆነ የሰው ኃይል ይኖረዋል የሚል መሆኑን አብራርተዋል» በሚል እንዲሻሻል::
- ገጽ 10 የመጀመሪያው ፓራግራፍ አራተኛ መስመር:- «ስለሆነም ጽ/ቤት ይኖረዋል የሚል ፅነሰ ሀሳብ በአዋጁ ውስጥ ቢኖርም በወቅቱ በሕገ መንግሥቱና በአዋጁ ሳይ ችግር ነበረባቸው በማለት አብራርተዋል» የሚለው ሙሉ በሙሉ እንዲወጣ:-
- ገጽ 12 ተራ ቁጥር 9 ሳይ ሁለተኛው መስመር:- «የበጀት ዕጥረት አለ ከተባለ .......... የጽ/ቤቱን አወቃቀር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ መስሎ አይታየኝም» የሚለው «..........አይታይም» በሚለው እንዲተካ የሚሉት ዋነኞቹ ሲሆኑ ስለ ወደፊት ቃለጉባኤ አያያዝን አስመልክቶ ሁለት አማራጮች ቀርበዋል:: እነዚህም በስም መጥቀስና ሳይጠቀስ መሠረተ ሀሳቡን ብቻ ማስፈር የሚሉት ሲሆኑ ቤቱም የግድ ካልሆነ በስተቀር በስም ሳይጠቀስ መሠረተ ሀሳቡን ብቻ ማስፈሩን መርጧል:: በመጨረሻም ቃለ ጉባኤውን በማፅደቅ ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሸጋግሯል::

## አጀንዳ 2. <u>የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የቆጠራ ካርታ ዝግጅት የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ ሪፓርት ማቅረብ</u>

ሪፓርቱ የቀረበው በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊ ሲሆን ግንቦት 12/95 በተደረገው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ ወቅት የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በያዘው ፕሮግራም መሠረት የመስክ ሥራው እንዲቀጥል ኮሚሽኑ በወሰነው መሠረት እየተሠራ መሆኑንና በውሳኔው መሠረትም በኮሚሽኑ ጽ/ቤትና በማ.ስ.ባ ቅ/ጽ/ቤቶች ሥራው መቀጠሉን በመግለጽ እስካሁን የተሠሩት ሥራዎች በአጭሩ እንደሚከተለው አብራርተዋል::

ከነዚህም ዋነኞቹ የቆጠራ ካርታ የካምፕና የመስክ መገልገያ ቁሳቁሶችን በማደራጀት በኩል የተከናወኑ የበጀት ድልድልና ሥርጭትን በተመለከተ፣ የቆጠራ ካርታ ሠራተኞች ቅጥርን፣ስምሪትና የቆጠራ ካርታ ሥራን ስለማስጀመርና ክትትል ማድረግን በተመለከተ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሥራዎች መሠራታቸውን በዝርዝር አቅርበዋል::

ከዚሁ በተጨማሪ በሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችንና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች በዝርዝር የገለጹ ሲሆን ለወደፊት ለሥራው መሳካት የኮሚሽኑ መመሪያና ትኩረት የሚያሻቸው

ጉዳዮችንም አብራርተዋል:: ከነዚሁም በዋነኛነት የማ.ስ.ባ የሥራ ትብብር እስከ ሰኔ 30/95 ብቻ የሚል ስለሆነ ለቀጣይ በጀት ዓመት መመሪያ እንዲሰጥበትም ጠይቀዋል::

በመጨረሻም የዕለቱ የኮሚሽኑ ስብሰባ የጽ/ቤቱን የእስካሁን እንቅስቃሴዎችን በመገምገም ወደፊት ጽ/ቤቱ ከሚጠብቀው ግዙፍ ሥራ አንጻር የማሻሻያ እቀጣጫዎችን እንደሚጠቀምና የሥራ መመሪያዎችን እንደሚያስተሳስፍ እንዲሁም ለተጠቀሱት ችግሮች ተገቢውን መፍትሔ በመፈለግ እንደሚጠናቀቅ እምነታቸው የፀና መሆኑን ገልፀዋል::

የኮሚሽኑ ሰብሳቢም በቀረበው የሥራ እንቅስቃሴ ሪፓርት ላይ ቤቱ እንዲወያይበት ጋብዘዋል:: ከቤቱም ያለውን እንቅስቃሴ በተጨባጭ የሚያሳይ ስለሆነና ከዚሁ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተዛመደ አጠቃላይ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው አጀንዳዎች በቀጣይነት ውይይት እንደሚካሄድባቸው በመገንዘብ ወደሚቀጥለው አጀንዳ መሸጋገሩ ደህና ነው የሚል ሀሳብ ቀርቧል:: በዚሁ ሀሳብ በመስማማት ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሸጋግሯል::

## አጀንዳ 3. <u>የኮሚሽኑ ጽ/ቤት አደረጃጀትና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት</u>

ይህን አጀንዳ አስመልክቶ ግንቦት 12/95 በተካሄደው የኮሚሽኑ አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ ወቅት ዘርዘር ያለና በቂ ማብራሪያ እንዲቀርብለት በወሰነው መሠረት የቀረበ ጥናት ነው::

በጽ/ቤቱ የቨይታል ስታቲስቲክስ መምሪያ ኃላፊ የቀረበው ይኸው አጭር ዘገባ አምስት ክፍሎች የያዘና 12 ገጾች ያለው ሲሆን እነዚህም የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንና የጽ/ቤት መቋቋም ሕጋዊ መሠረት፣ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅርና ሥልጣንና ተግባር፣ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የሰው ኃይል ድልድል አፈጻጸምና አሠራር፣ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከማ.ስ.ባ ጋር የሚኖረው/ለለአለው አደረጃጀትና የሥራ ግንኙነት የሚሉት ዋነኞቹ በአቅራቢው ማብራሪያ የተሰጠባቸው አርዕስቶች ነበሩ::

በአጭሩም የኮሚሽኑ ጽ/ቤት መቋቋም ሕገመንግሥታዊ ይዘት እንዳለው፣ በማቋቋሚያ አዋጁም ለጽ/ቤቱ ተሰይተው የተሰጡት የሥራ ኃላፊነቶች እንዳሉት፣ በዚሁ መነሻም በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትና በሚኒስትሮች ም/ቤት በተሰጠው መመሪያ መሠረት በ1995 በጀት ዓመት በተፈቀደለት በጀት ሠራተኞችን በማሰልጠንና ወደ መስክ በማሰማራት የቆጠራ ካርታ ሥራውን መጀመሩን አብራርተዋል::

ከዚሁ በተጨማሪ የጽ/ቤቱ የ1995 ዓ.ም በጀት በተጠየቀበት ወቅት የሚኒስትሮች ም/ቤት በህዳርና በታህሣሥ ባካሄዱት ስብሰባ የካርታ ሥራው የአስተዳደርና የቴክኒክ አሠራርን አስመልክቶ የማ.ስ.ባ ቅ/ጽ/ቤቶች የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በክልል ስሚያከናውናቸው ተግባራት አገዛ እንዲያደርግ መመሪያ እንደተሰጠውና በዚሁ መሠረትም በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ስም የባንክ አካውንት በየቅ/ጽ/ቤቶች መከፈቱ፣ የፋይናንስ ክፍያዎች በመፈፀም በኩል፣ የሰው ኃይል በመቅጠርና በማስተዳደር የጽ/ቤቱን ንብረት በመያዝና በማሰራጨት በኩል አገዛ በማድረግ ላይ መሆኑን የገለጹ ሲሆን በቆጠራ ውጤቱ ማ.ስ.ባ በናሙና መረጣ በኩል ከፍተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ የቆጠራ ካርታ ሥራው ስግንኙነቱ መነሻ መሆኑን ጠቀመዋል።

በዚሁ በቀረበው ማብራሪያ ላይ አስተያየትና ጥያቄ ካለ በሚል ቤቱ እንዲወያይበት ሰብሳቢው ጋበዘዋል። በዚህ መሠረት በወቅቱ የቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የሚከተሉት ነበሩ።

1. በቀረበው ሪፓርት በገጽ 11 የማ.ስ.ባ ስሚሰራቸው ሥራዎች ስሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ስናሙና መረጣ የሚጠቀምበትን የቆጠራ ካርታ ሥራ እየተቆጣጠረ በባለቤትነት መሥራት ግዴታ ስለሚሆንበት ጭምር ነው የሚለው መሠረተ ሀሳብ ምን ማለት ነው?

2. የማ.ስ.ባ መኪና ደስጥ ከሚባል በኮንትራት ስምን አይሰራውም?

3. የመኪና ዕጥረት መኖሩ እየተገለፀና የታቀደው በጀት አነስተኛ መሆኑ እየተጠቀሰ የሥራው ሁኔታ እንዴት ይታያል? የሚሉት ዋነኞቹ ጥያቄዎች ናቸው።

ከኮሚሽኑ አባላትና በስብሰባው በተገኙ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች የሚከተሉት መልስና አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

1. የማ.ስ.ባ በባለቤትነት ስሜት መሳተፍ አለበት ሲባል ስሚሰራቸው ሥራዎች በአብዛኛው ስናሙና ፍሬምነት ስለሚጠቀምበትና በሥራው ሂደት የመሳተፍ እና የመተባበር ግዴታ እንዳለበት ይህም በበላይ አካልም አጽንኦት የተሰጠው መሆኑን፣

2. የቆጠራ ካርታ ሥራ በኮንትራት የሚሰጥ ተግባር ሳይሆን በሙያው በተካኑ ሠራተኞች በከፍተኛ ጥንቃቄ መሠራትና ተጠያቂነት ባለው ተቋም መሠራት ያለበት መሆኑን፣

3. በትክክል ከታየ የመኪና ዕጥረት አለ ለማለት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም በማ.ስ.ባ ያሉት ተሽከርካሪዎች በበቂ ለመጠቀም ካለመቻሉም በላይ ከሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ትብብር አልተጠየቀም:: በሌላም በኩል በበጀት ዕጥረት ምክንያት ሥራው በዝግታ ረዘም ላለ ጊዜ ቢሰራም ቀደም ብለው የተሰሩ ካርታዎች በድጋሚ ለማደስና ይህም ተጨማሪ ወጪ ስለሚኖረው በጊዜ፣ በገንዘብና በሰው ኃይል አኳያ መታሰብ ያለበት መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ለጊዜው የሁለቱ መ/ቤቶች አደረጃጀትና አወቃቀር ቀጥሎ ከሚቀርበው አጀንዳ በኋላ ሲቀርብ የሚችል በመሆኑና ቤቱም በዚሁ በመስማማት ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሸጋግሯል::

## አጀንዳ 4. <u>በ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራንና ሕዝባዊ ምርጫን በአንድ ወቅት ማካሄድን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት</u>

የአጀንዳው መነሻ የሆነው ግንቦት 12/95 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ባካሄደው አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ ወቅት ካሳለፈው የውሳኔ ሀሳብ ማለትም በመንግሥት በኩል በ1997 ዓ.ም የሕዝብና ቤት ቆጠራንና የሕዝባዊ ምርጫን የሚያክሉ ሁለት ታላላቅ ሥራዎች በአንድ ወቅት (በ1997 ዓ.ም) ማካሄድ አይቻልም የሚል አቋም እስካለ ድረስ ዘርዘር ያለ ሀሳብ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የሚልና ስለውሳኔ ሀሳብም በክቡር ዶ/ር ሙሳቱ ተሾመ እና በዶ/ር አብዱሳሂ ሀሰን በኩል ዝርዝር ማብራሪያ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በተወሰነው መሠረት ነው::

በዕለቱም 10 ገጽ የያዘ ጽሑፍ ተጠናቅሮ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም በሀገራችን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ታሪክ፣ ቀደም ሲል የተካሄድት ሁለት የሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም፣ ለሦስተኛ ጊዜ በ1997 ሲካሄድ የታቀደው የቆጠራ ሥራና ሥራውን ለማስፈጸም በቋሚነት የተቋቋመው ጽ/ቤት ያስከተለው ችግር እንደዚሁም የኮሚሽኑ አደረጃጀት ያለበት ችግርና የመፍትሔ ሀሳቦችን አካቷል::

በዚሁ ማብራሪያ ወቅት የቀረቡት ነጥቦች ሲጠቃለሉ፣

- በድርቅና ይህን ተከትለው በሚመጡ የሰፈራ ፕሮግራምና በድርቅ የተጐድትን ለመደጐም በሚደረገው ጥረት በሀገሪቱ የበጀት ዕጥረት መኖሩ፣
- በሀገሪቱ ውስጥ በ1997 ዓም ሕዝባዊ ምርጫ እንደሚካሄድና ይህም ግዙፍ ወጪ እንደሚያስከትልና ማሸጋሸግ እንደማይቻል፣ ቆጠራውም እንደዚሁ ግዙፍ ወጪ ስለሚጠይቅና ከሌሎች ሀገሮች ልምድም ማስተላለፍ እንደሚቻል፣
- የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ለ1996 በጀት ዓመት ከጠየቀው ብር 45,643,000 ውስጥ በአስፈጻሚ መ/ቤት (በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር) በኩል የተደገፈው ብር 10,000,000 ብቻ መሆኑ

ይህም በሚኒስትሮች ም/ቤት ከሀገሪቱ በጀት ጋር እንዲጸድቅ ወደ ተወካዮች ም/ቤት እንደተላከ እና በዚህ አነስተኛ በጀት ቀደም ሲል በታቀደው መሠረት መንዝ እንደማይቻል እና ሥራው ከተፈቀደው በጀት አንጻር መስተካከል እንደሚኖርበት፣

- ፓርላማው በጀት ጨምሮ ቢያፀድቅም እንኳን አስፈጻሚው መ/ቤት ገንዘብ የለኝም ካለ ምንም ማድረግ እንደማይችል፣
- ቆጠራው ይራዘም ከሚለው ጋር ተያይዞ የጽ/ቤቱ አወቃቀርና አደረጃጀት በምን መልክ መሆን እንዳለበትና በማ.ስ.ባ እና በጽ/ቤቱ በኩል የሚኖረው ግንኙነት እንዲታሰብበት የሚሉት ናቸው::

በአጠቃላይ በተሰጠው ገለጻ ቀደም ሲል ሰልፕነው ለቆጠራ ካርታ ሥራው ወደ መስከ የተሠማሩ ቡድኖችን በመቀነስ ቆጠራው በአንድ ዓመት ወይም በሁለት ዐመት ቢራዘም ፓርላማውም፣ አስፈጻሚውም ሆነ ብዙ መቀመጫ ያለው ፓርቲም ቢሆን ይህን ያከል የተቃረነ አቋም ይኖራል ተብሎ እንደማይገምት ተብራርቷል:: ከኮሚሽኑ አባላትም የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል:: ከነዚሁም ዋነኞቹ፣

- የቀረበ ሪፓርት ትክክለኛና ወቅታዊ የሀገሪቱ ችግር የሚያንፀባርቅ ስለሆነ ተሸጋሽጐ ሥራው ወደፊት ቢሠራ የተሻለ መሆኑን፣
- ሁለት ግዙፍ ሥራዎች በአንድ ላይ ማካሄድ በሥራም ሆነ በበጀት ላይ ጫና ያለው መሆኑ፣
- ይተሳሰፍ ሲባል ሥራው ይቀም ማለት ሳይሆን በአነስተኛ የሰው ኃይል እና በአነስተኛ ወጪ በዝግታ መሠራት እንዳለበት፣
- ቆጠራው በመሸጋሸጉ ከታመነበት ማን እንደሚያካሂደው መገለጽ እንዳለበትና የ1996 ዓ.ም የማ.ስ.ባ ድጋፍ ትብብር እስከ ሰኔ 30/95 ብቻ ስለሆነ አንድ ውሳኔ ማግኘት እንዳለበት፣ የሚሉት ዋነኞቹ ከአባላቱ የቀረቡ ማብራሪያዎች ናቸው::

በሌላ በኩል በጽ/ቤቱ ዋና ፀሐፊና በስብሰባው በተገኙ ኃላፊዎች የሚከተሉት የተቃውሞ ሀሳቦች ቀርበው ነበር:: ከእነዚህም ዋነኞቹ፣

  - ለ1996 በጀት ዐመት ጽ/ቤቱ ካቀረበው ብር 45 ሚሊዮን ውስጥ 10 ሚሊዮን ብቻ ተፈቀደ የሚለው ትክክል እንዳልሆነ ይኸውም በተለያዩ ወቅቶች በተደረጉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና በተወካዮች ም/ቤት የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል ተነጋግረን የተደገፈው ብር 40 ሚሊዮን እንደነበረ ይህም ከጽ/ቤቱ እውቅና ወጪ የተፈፀመና ትክክለኛ መስመሩን ያልተከተለ ጉዳይ መሆኑ፣አሁንም ከተወካዮች ም/ቤት ከበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር ውይይት እየተደረገበት ስለሆነ እንደፀደቀ መናገር እንደማይቻል፣

- ይሸጋሸግ ቢባል እንኳን በ1995 በጀት ዓመት ለካርታ ሠራተኞች ሥልጠና፣ መስክ ለተሰማሩ ከ1000 በላይ ሠራተኞች የደመወዝና የአበል፣ ለነዚሁ ሠራተኞች የአሳቂና የቋሚ ዕቃ ግዢና ሥርጭት ግዙፍ ወጪ ስኪሣራ የሚደርግ መሆኑን፣ ይህም ማለት ከ11 ሚሊዮን ብር በላይ ከመባከኑም በላይ የሚያስከትለው የማህበራዊና ፓለቲካዊ ውዝግብ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል፣
- የቆጠራ ካርታ በአጭር ጊዜ ካልተሰራ በስተቀር ጊዜው በረዘመ ቁጥር (Outdated) እንደሚሆንና መከለስ (update) የግድ እንደሚሆንና ለዚሁም ከፍተኛ ወጪ እንደሚያስከትል፣
- በተሸጋሸገ ቁጥር የመረጃ ውጤት ለተጠቃሚ ሕብረተሰብ የሚቀርብበት ጊዜ እንደሚያራዝምና ይህም በመንግሥትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በኩል ለሚታሰሙ የአጭርና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን እንደሚጐዳ፣
- የማሸጋሸጉ አማራጭ ሀሳብ የጽ/ቤቱ ሀሳብ ስላልሆነና የቆጠራው ጊዜ መራዘም ሕገመንግሥታዊ ይዘት ያለው ስለሆነ ችግርም ካለ ለማሸጋሸጉ በጽ/ቤቱ በኩል በአጠቃላይ ሙያዊ ትንተና ሳይቀርብ ሲወሰድ የታሰበ እርምጃ ስለመሆኑ የሚሉት በወቅቱ የቀረቡ ዋነኞቹ የተቃውሞ ሀሳቦች ነበሩ::

በመቀጠልም ቤቱ በሰፊው ከአብላላው በኋላ ፕሮፓዛል ለተወካዮች ም/ቤት እንዲቀርብና ውሳኔ እንዲሰጥበት ተስማምቷል::

ስለሆነም ከላይ የተዘረዘሩትን ማብራሪያዎችና አስተያየቶች ከገመገመ በኋላ የጋራ ውሳኔ ላይ የደረሰባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

1. ኮሚሽኑ በአንደኛ አስቸኳይ ስብሰባው ወቅት በ1997 ሊካሄድ የታቀደውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ወደ 1998 ወይም 1999 እንዲራዘም ሀሳብ መቅረቡና በወቅቱም ተጨባጭ ምክንያት ተጠንተው እንዲቀርቡ በተወሰነው መሠረትና በዚሁ በቀረበው ጽሑፍ መነሻም:-
   - በ1997 ሁለት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ማለትም የሕዝብና ቤት ቆጠራውና የሕዝባዊ ምርጫ ፕሮጀክቶች በአንድ ላይ ማካሄዱ ብዙ ወጪ ስለሚጠይቅና ሕዝባዊ ምርጫውንም ማራዘም እንደማይቻል በመገንዘብ እና በሀገሪቱም አሁን ባለው የበጀት እጥረት ምክንያት የሕዝብና ቤት ቆጠራው እስከ 1999 እንዲዘገይ::

2. ይህ የውሳኔ ሀሳብ ሥራው ይቁም ማለት ስላልሆነ ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የዝግጅት ተግባራት አንዱ የሆነውን የቆጠራ ካርታ ሥራ በተራዘመ መንገድ በተፈቀደው በጀት መሠረት ሥራው እንዲቀጥል እንዲደረግ እና፣

3. የቆጠራውን ሥራ በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወን ይቻል ዘንድ የጽ/ቤቱ አደረጃጀትና አወቃቀር በዋነኛነት በቆጠራው የዕለት ተዕለት አፈጻጸም አስተዳደራዊና ኦፕሬሽናል ሥራዎች በማይሰማራበት አግባብ እንዲሆንና የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና በተወካዮች ም/ቤት እንዲታይ የሚሉት ሦስቱ የውሳኔ ሀሳቦች ናቸው።

እነዚሁ የውሳኔ ሀሳቦች ከቃለጉባኤው ጋር አባሪ በማድረግ በሸኚ ደብዳቤ ለተወካዮች ም/ቤት እንዲደርስ የተስማማ ሲሆን ከሥራው ጋር በተያያዘ የጽ/ቤቱንና የማ.ስ.ባ በ1995 ዓ.ም የተጀመረው ትብብር ከላይ የተዘረዘሩት የውሳኔ ሀሳቦች ውሳኔ እስከሚያገኙ ድረስ እንዲቀጥል በድጋሚ አስገንዝበዋል።

## አጀንዳ 5. አማራጭ የሕዝብ ቆጠራ አሠራርን በተመለከተ

አጀንዳው በዕለቱ እንዲቀርብ መነሻ የሆነው ግንቦት 12/95 የኮሚሽኑ አባላት ባካሄዱት አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ ወቅት ከተላለፉት የውሳኔ ሀሳቦች ውስጥ በ3ኛ ደረጃ የሚገኘው ማለትም «ለኮሚሽኑ የተለያዩ አማራጮችን ማቅረብ ይቻል ዘንድ በአቶ አሰፋ ብሩ የሚቀርበው አማራጭ የቆጠራ ካርታ አግባብና በዚሁም ላይ ከጽ/ቤቱም ሆነ ከማ.ስ.ባ ባለሙያዎች የሚቀርቡ ሙያዊ አስተያየቶች ታክለውበት እንዲቀርብ» ከሚለው አንጻር የቀረበ ሲሆን ለዚሁም በተከበሩ አቶ አሰፋ ብሩ በኩልም ሆነ በሌሎች የማ.ስ.ባ እና የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች የድጋፍና የተቃውሞ ጥናቶች በማካሄድ ተገቢውን ማብራሪያ ለመስጠት የሚያስችሉ ደጋፊ ማስረጃዎችና ጽሑፎች ቀርበው ነበር።

ሆኖም ከጊዜ እጥረት አንጻር በሌላ የኮሚሽኑ ስብሰባ ወቅት ሊቀርብ እንደሚችል በምርጫ ቦርድ ኃላፊው በኩል በቀረበው ሀሳብ መሠረት ቤቱ በመስማማቱ ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሸጋግሯል።

## አጀንዳ 6. የቆጠራ ካርታ ሥራ የፋይናንስ ጥያቄና የመስክ ሥራ አደረጃጀት

በዚህ አርዕስት ላይ ሪፓርት ያቀረቡት የጽ/ቤቱ የቴክኒክ መምሪያ ኃላፊ ሲሆኑ ከቤቱም ከላይ ከተሰጡት የጋራ ውሳኔዎች አንጻር አጀንዳው ይቅረብ ወይስ አይቅረብ የሚሉ ሀሳቦች ነበሩ:: ሆኖም የሚቃረኑ ሀሳቦች ካሉ ማስቀረት ስለሚቻል በተቻለ መጠን በአጭሩ እንዲቀርብ ተስማምቷል::

በዚሁ መሠረት የቀረበው ሪፓርት 12 ገጽ የያዘና የቆጠራ ካርታ የፋይናንስ ፍላጐት፣ የሰው ኃይልና አጠቃቀም፣ የቆጠራ ካርታ አሠራር ሁኔታ፣ የካምፕና የመስክ መገልገያ ዕቃዎች ግዢና ስርጭት ሁኔታ፡ ወጪዎችን ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች እና እንደ አማራጭ በክልሎች የተሰበሰበ የG.I.S መረጃዎች ለቆጠራ ካርታ ሥራ መጠቀምን አስመልክቶ ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል::

በተለይም በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አንደኛ መደበኛ ስብሰባ ወቅት በክልሎች የተሰበሰቡ የG.I.S መረጃዎች ለቆጠራ ካርታ ሥራ ምን ያህል ሊያግዙ እንደሚችሉ እንዲጣራ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያና የደቡብ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የሚመለከታቸው ቢሮዎችን አነጋገረን በተገኘው መረጃ መሠረት በትግራይ በኩል በርካታ መረጃዎች እንደተሰበሰቡ በሌሎች ግን በጅምር ላይ በመሆናቸው ይህም ለወደፊት በጥናት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ እንደሚደረግላቸውና የሚጠቅመውን መውሰድ እንደሚቻል አስረድተዋል::

እስካሁን የተከሰቱ ችግሮችን ሲገልጹም በተለይ የመንገድ መሪዎችን በተመለከተ በተዋረድ መመሪያ እንዲሰጥበት፣ የቀበሌ የድንበር አለመግባባቶችን አስመልክቶ በኮሚሽኑ አባላት በኩል ስተዋረድ የአስተዳደር አካላት መመሪያ የሚያስፈልገው ስለሆነ ችግሩን ለመፍታት ጥረት መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል::

ከቤቱም የተለያዩ ሀሳቦች የቀረቡ ሲሆን የመንገድ መሪን በተመለከተ በተዋረድ መመሪያ እንዲሰጥና በማስሚድያም ማስተዋወቅ ብሎም እስካሁን ችግሮቹ የተከሰተባቸው ቦታዎች ተለይተው እንዲቀርቡ ተስማምቷል:: የድንበር አለመግባባትን በተመለከተ በአንዳንድ ክልሎች የጉዳ ሽማግሌዎችን በመያዝ እንዲፈታ ጥረት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ተገልጿል::

በአጠቃላይ በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ ዓላማውን በመግለጽ ማስረዳትና ሥራው እስከሚጠናቀቅ የትብብር ደብዳቤ ወደታች ለማውረድ ጥረት ይደረጋል በማለት ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሸጋግሯል።

## አጀንዳ 7. በቆጠራ ካርታ ቀጣይ ተግባር የኮሚሽኑን የሥራ መመሪያ የሚጠይቁ ጉዳዮች

ከቆጠራ ካርታ ሥራው ጋር በተያያዘ ያጋጠሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ እነዚሁም የኮሚሽኑ መመሪያ የሚጠይቁ ችግሮች/ነጥቦች የቀረበበት አጀንዳ ሲሆን የቀረበውም በዋና ፀሐፊው ነበር። ከነዚሁ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ፣

- የማ.ስ.ባ የትብበር/ድጋፍ ሁኔታ እስከ ሰኔ 30/95 ድረስ ብቻ ስለሆነ በ1996 በጀት ዓመት ሥራው በምን መንገድ መቀጠል እንዳለበት መወያየትና ውሳኔ መስጠት፣
- የተሽከርካሪ ዕጥረት የቆጠራ ካርታ ሥራው በታቀደው መሠረት እንዳይሰራ እያደረገው ስለሆነ ተሽከርካሪ የሚገኝበትን ሁኔታ ቢመቻች ወ.ዘ.ተ ናቸው።

ከቤቱ የተሰጡ ምላሾችም የሚከተሉት ነበሩ።

- የማ.ስ.ባ ትብብርና ድጋፉን በተመለከተ ከላይ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መፍትሔ እስከሚያገኝ ድረስ እስካሁን ባለበት ሁኔታ እንዲቀጥል

በመጨረሻም የውሳኔ ሀሳቦቹ ከዕለቱ ቃለ ጉባኤ ጋር በሽኚ ደብዳቤ በቀጥታ ለም/ቤቱ እንዲደርስ ተስማምቶ የዕለቱ ስብሰባ በ11:00 ሰዓት አብቅቷል።